# የ St Dominic Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን የመዝጋት እቅድን በተመለከተ የተደረገ ምክክር

ማጠቃለያ

በ31 ኦገስት 2025 የ St Dominic Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን የመዝጋት እቅድን በተመለከተ እርስዎን እያማከርን ነው። ይህ ትምህርት ቤቱን ወደመዘጋት ሊያመራ የሚችል ልንከተለው የሚገባን የሂደቱ የመጀመሪያ ደረጃ ነው።

ከቅርብ አመታት ወዲህ በ Hackney እና በብዙ የ London ክፍሎች እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች ብዛት ቀንሷል። ከዚህ ጀርባ ያሉት ምክንያቶች ዝቅተኛ የወሊድ መጠኖች፣ ለቤተሰቦች ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት እጥረት፣ እንዲሁም ዩናይትድ ኪንግደም መውጣት (Brexit) እና በቅርብ ጊዜ የተከሰተውን ወረርሽኝ ያአትታሉ ተብሎ ይታሰባል። የህጻናት ብዛት መቀነሱ ከፍተኛ ብዛት ያለው ትርፍ የትምህርት ቤት ቦታዎች እንዲኖሩ እና ከማዕከላዊ መንግስት የሚሰጠው የገንዘብ መጠን እንዲቀንስ በማድረጉ ትምህርት ቤቶቻችን አስቸጋሪ ፈተናዎችን እየተጋፈጡ ነው።

በ2014 በ Hackney ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጀመሩ 2846 ልጆች ነበሩ። በሜይ 2024፣ ይህ ቁጥር በይፋ ተመዝግበው የመጀመሪያ አመት ትምህርት የሚማሩ ህጻናት ወደ 2203 ቀንሷል - በ23% ቀንሷል። ይህ 577 የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ቦታዎችን ክፍት ትቷል (ሜይ 2024) - ከ19 ባዶ የመማሪያ ክፍሎች ጋር እኩል ነው።

ትምህርት ቤቶች በምዝገባ ዝርዝራቸው ላይ ላለው እያንዳንዱ ልጅ ከመንግስት ገንዘብ ይቀበላሉ። የእያንዳንዱ ያልተሞላ የትምህርት ቤት ቦታ አመታዊ ዋጋ በግምት £6,000 ነው። በ Hackney የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉት ያልተሞሉ ቦታዎች ብዛት እየጨመረ በመምጣቱ የገንዘብ ጫናው እየጨመረባቸው ነው። የገንዘብ ድጋፉ በመቀነሱ፣ ብዙ ትምህርት ቤቶች በብቃት መስራት ወይም ለህጻናት የሚዘጋጁ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያሉ ጉዞዎች እና ጉብኝቶች፣ ከትምህርት ሰአት በኋላ የሚደረጉ ክበቦች እና ውድድሮች የመሳሰሉ አስደሳች ተግባራትን ማቅረብ አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተውታል። ምክር ቤቱ ቀጣይነት የሌላቸውን ትምህርት ቤቶች በገንዘብ መደገፍ አይችልም እንዲሁም ትምህርት ቤቶቻችን ለወደፊት ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና Hackney የምትታወቅበትን ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለመጠበቅ ከባድ ውሳኔዎችን መወሰኑን መቀጠል አለበት።

ባለፈው የትምህርት ዘመን (2023/24) አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት አስቸጋሪ ውሳኔ ለመወሰድ ተገደናል። በጁላይ 2024 ተዘግተዋል። ይህን ውሳኔ ያስተላለፍነው ክፍት እንዲሆኑ እና ትምህርት ቤቶቹ በፋይናንስ ደረጃ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው በጣም ጥቂት ልጆች በመኖራቸው ነበር። እነዚህ ውሳኔዎች በፍጹም ቀላል የሚባሉ ባይሆኑም ውሳኔዎቹን ያስተላለፍነው በ Hackney ውስጥ ጠንካራ የትምህርት ስርዓት ከመፍጠር አላማ ጋር የሁሉንም ልጆች ተጠቃሚነት ታሳቢ በማድረግ ነው። ሌሎች የለንደን ምክር ቤቶችም ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት እና ለማዋሃድ ከባድ ውሳኔዎችን በሚወስኑበት ጊዜ ተመሳሳይ ፈተናዎች እያጋጠሟቸው ነው።

በሚያሳዝን ሁኔታ በ Hackney የቀድሞ ትምህርት ቤት ቢዘጋም አሁንም እነሱን ለመሙላት ካሉን ልጆች የበለጠ ወሳኝ የትምህርት ቤት ቦታዎች አሉን። በ Hackney ትምህርት ቤቶች በይፋ ተመዝግበው የመጀመሪያ አመት ትምህርት የሚማሩ ህጻናት 2125 ነበሩ (17/9/2024) ነገር ግን እኛ 2675 ቦታዎች

አሉን። ይህ ማለት በዚህ ሴፕቴምበር ወር (2024) 550 ትርፍ ቦታዎች (21%) ነበሩን ይህም ለትምህርት ቤቶቻችን ቀጣይነት ያላቸው የገንዘብ ድጋፍ ፈተናዎችን አስከትሏል።

እርስዎን እያማከርን ያለነው ለምንድን ነው?
ግባችን እያንዳንዱ ልጅ ሰፊ እና የበለጸገ የትምህርት ተሞክሮን የሚያገኝበት ጠንካራ የትምህርት ስርዓት መፍጠር ነው። ይህ ሊሳካ የሚችለው ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን በታቀደው የቅበላ ፈቃድ ቁጥራቸው (PAN) ውስጥ ብዙ ልጆችን መቀበል እና የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ ከፍ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ ለተወሰኑ የHackney የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የሚማሩ ልጆች ብዛት በጣም ሆኖ ቀጥሏል እንዲሁም በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ምክር ቤቱ ማስተዳደር የማይችላቸውን የገንዘብ እጥረቶች አስከትሏል።

ይህ በ St Dominic Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከሰተ ሲሆን አሁን የትምህርት ቤቱን መዘጋት ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። የተሻለ አማራጭ ሊኖር እንደሚችል ብናስብ ይህን አናደርግም ነበር።

አሁን በ31 ኦገስት 2025 የ St Dominic Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን (Ballance Rd, E9 5SR) ለመዝጋት የቀረበው እቅድ ላይ ያሉዎትን አስተያየቶች መስማት እንፈልጋለን። ስለ ትምህርት ቤቱ የወደፊት ሁኔታ ሊኖርዎ የሚችሉትን ሃሳቦች እና/ወይም ተለዋጭ አማራጮችን እንቀበላለን። ትምህርት ቤቱ ለልጆች፣ ለወላጆች/ተንከባካቢዎች፣ ለሰራተኞች እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ለመረዳት ስለሚያግዘን የእርስዎ አስተያየት፣ ጥቆማቆች እና ግብረመልስ አስፈላጊ ናቸው።

የ **St Dominic Catholic** አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
የSt Dominic በ Ofsted (2023) 'ጥሩ' ተብሎ በይፋ የታወጀ ባለ አንድ ክፍል ትምህርት ቤት ነው። ከቅርብ አመታት ወዲህ፣ ትምህርት ቤቱ በተመዝጋቢዎች ዝርዝር መቀነስ ተጽዕኖ አድሮበታል፣ በዚህ ምክንያት፣ በ2022 ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል የታቀደ የቅበላ ቁጥር በእያንዳንዱ አመት ከባለ ሁለት ክፍል ትምህርት ቤት (በየአመቱ 60 ተማሪዎች) ወደ ባለ አንድ ክፍል ትምህርት ቤት (በየአመቱ 30 ተማሪዎች) ቀንሷል።

ባለፈው አመት የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል፣ ትምህርት ቤቱ በተመዝጋቢዎች ዝርዝር ላይ በግምት ከ30 ቦታዎች 16 ልጆች ነበሩት፣ ሰንጠረዥ 1ን ይመልከቱ።

ሰንጠረዥ **1 -** የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል የተመዝጋቢ ዝርዝር ቁጥር **2023/24 (**የሜይ ቆጠራ**)**

| PAN (የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል) | በተመዝጋቢ ዝርዝር ላይ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር (የመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል) | ትርፍ ቦታዎች | % የ PAN ትርፍ |
|---|---|---|---|
| 30 | 16 | 14 | 47% |

በሜይ 2024፣ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 2 ላይ እንደሚታየው ትምህርት ቤቱ በግምት ከ360 ቦታዎች ከመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል እስከ 6ኛ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል ያሉ 230 ተማሪዎችን መዝግቧል።

ሠንጠረዥ **2 -** የሙሉ ትምህርት ቤት የተመዝጋቢ ዝርዝር **2023/24** (የሜይ ቆጠራ)

| የታቀደ የቅበላ ቁጥር (PAN) (ሙሉ ትምህርት ቤት) | በተመዝጋቢ ዝርዝር ላይ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር (ሙሉ ትምህርት ቤት) | ትርፍ ቦታዎች | % የ PAN ትርፍ |
|---|---|---|---|
| 360 | 230 | 130 | 36% |

ከ 17/9/2024 ጀምሮ፣ በመጀመሪያ አመት ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ የተመዘገቡት 23 ልጆች ብቻ ናቸው።

ይህንን ትምህርት ቤት ለመዝጋት ያቀድነው ለምድን ነው**?**
ምንም እንኳን St Dominic በ Ofsted 'ጥሩ' ተብሎ በይፋ የታወጀ ትምህርት ቤት ቢሆንም፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተመዝጋቢ ዝርዝሮች መቀነስ አጋጥሞታል። ትምህርት ቤቱ 420 ህጻናትን መቀበል በሚችል ህንጻ ውስጥ ይገናኛል ነገር ግን ትምህርት ቤቱ በቂ ቦታ መሙላት የቻለው ግማሽ ያህሉን ብቻ ነው። በኦክቶበር 2021 እና 2023 ቆጠራዎች መካከልበተመዝጋቢ ዝርዝር ላይ ያለው የተማሪዎች ብዛት በ 18% ቀንሷል።

የትምህርት ቤቱን የፋይናንስ አቋም እና ለወደፊት ቀጣይነት ያሉትን ዕቅዶችን በመገምገም፣ ምክር ቤቱ ትምህርት ቤቱ ለልጆቹ የሚቀርበውን የትምህርት ጥራት አደጋ ላይ ሳይጥል እና ከፍተኛ የፍላጎት ደረጃ ባላቸው ልጆች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሳያሳድር መቆየት እንደማይችል አምኗል።

ከ St Scholastica አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Kenninghall Road, E5 8BS) ጋር የመዋሃድ እድል ግምት ውስጥ ገብቶ ነበር ነገር ግን በትምህርት ቤቶቹ መካከል ያለው ርቀት በጣም ሩቅ እንደሆነ ታስቧል። ስለዚህ ትምህርት ቤቱን የመዝጋት እቅድን በሚመለከት ምክክር ሊጀመር ይገባል።

ለልጆቹ ምን ማለት ነው**?**
ሁሉም በተመዝጋቢ ዝርዝር ላይ ያሉ ልጆች በቤታቸው አካባቢ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ቦታ ይሰጣቸዋል። ቤተሰቦች ምርጫቸው ከሆነ ወደ ሌሎች የካቶሊክ ትምህርት ቤቶች እንዲዛወሩ ለመርዳት ምክር ቤቱ ከሮማ ካቶሊክ የዌስትሚኒስተር ደብር (Roman Catholic Diocese of Westminster, RCDOW) ጋር በቅርበት ለመስራት አቅዷል። በጣም ቅርብ የሆኑት አማራጭ የሮማ ካቶሊክ ትምህርት ቤቶች St Elizabeth Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Tower Hamlets) እና St Scholastica Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Hackney) ሲሆኑ ሁለቱም ከ St Dominic በግምት በ 35 ደቂቃ ርቀት ላይ ይገኛሉ።

የትምህርት፣ የጤና እና የእንክብካቤ እቅድ (EHCP) ያላቸው ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦችን ልዩ ድጋፍ የሚያገኙ ልጆች ካላቸው ቤተሰቦች ጋር በዝውውሩ ድጋፍ ለማድረግ በቀጥታ በምክር ቤቱ የልዩ ትምህርት ፍላጎቶች አገልግሎት እገዛ የሚያገኙ ይሆናል። በሂደት ላይ ያሉ የEHCP ማመልከቻዎች ከእቅድ አስተባባሪዎች በተገኘ ድጋፍ መገምገማቸውን የሚቀጥሉ ይሆናል።

ለልዩ ትምህርት ፍላጎቶች እና የአካል ጉዳቶች ድጋፍ የሚያገኙ ተማሪዎች ቤተሰቦች የሆኑ ነገር ግን EHCP የሌላቸው አቅርቦት ወይም ቅንብሮች ላይ ለውጦችን ማድረግ ሲያስቡ ምክር እና መመሪያ የሚያገኙ ይሆናል። ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ ለማቅረብ ልዩ የአካባቢ ባለስልጣን ሰራተኞች አሉ።

አዳዲስ ጓደኞችን የማፍራት እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የመሞከር እድሎች ላይ ትኩረት አድርገን የትምህርት ቤቱን ለውጥ በተቻለ መጠን ምቹ እና አወንታዊ በማድረግ የእያንዳንዱ ልጅ ስሜቶች በአግባቡ ግምት ውስጥ መግባታቸውን ለማረጋገጥ ከትምህርት ቤት አመራሮች ጋር በቅርበት የምንሰራ ይሆናል።

ለልጄ ልዩ እና ምናልባትም ትልቅ የሆነ ትምህርት ቤት አካል መሆን ምን ማለት ነው?
ለአንዳንድ በ St Dominic ለሚማሩ ልጆች ወደ ሌላ እና ምናልባትም ትልቅ ወደሆነ ትምህርት ቤት መሄድ ከባድ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን። አዲሱ ትምህርት ቤት ለልጅዎ(ጆችዎ) የተለየ ስሜት የሚፈጥር ቢሆንም፣ በፍጥነት መረጋጋት እንዲችሉ ትክክለኛውን ድጋፍ እንደሚያገኙ እናረጋግጣለን። ግምት ውስጥ በገቡት አማራጮች ላይ የልጆችን አስተያየት መስማት እንፈልጋለን ስለዚህ ሀሳቦቻቸውን እና ስሜቶቻቸውን በመሰብሰብ ትምህርት ቤቱ እንዲረዳን እንጠይቃለን።

የቅበላዎች ሂደት የሚሰራው እንዴት ነው?
አማራጭ የትምህርት ቤት ቦታዎች ላይ ለማመልከት እንዲሁም ያሉብዎትን ማናቸውንም ችግሮች እና ስጋቶች ግምት ውስጥ በማስገባት አንድ የተመደበ የቅበላ መኮንን መረጃ እና ድጋፍ በመስጠት ያግዝዎታል። ሌሎች ትምህርት ቤቶች ላይ የማመልከት እና በማንኛውም ጊዜ ልጅችዎን የማዘዋወር መብት አለዎት።

የትምህርት፣ የጤና እና የእንክብካቤ እቅድ (EHCP) ያላቸው ልጆች ካሉዎት በአጋጣሚ ምክር ቤቱ በኤፕሪል 2025 St Dominicን ለመዝጋት ከወሰነ ስለሚመርጧቸው አማራጭ ትምህርት ቤቶች ውይይት ለመጀመር በተቻለ ፍጥነት የምናነጋግርዎ ይሆናል። መዘጋቱ የሚፈጸምበት የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች 'የጊዜ ስሌዳ' ተብሎ በሚጠራው ሠንጠረዥ ላይ ይታያል።

ለሰራተኞች እና ለርዕሰ መምህር ምን ማለት ነው?
የ St Dominic መዘጋት ርዕሰ መምህሩን ጨምሮ በሁሉም ሰራተኞች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ምክር ቤቱ አዳዲስ የስራ ድርሻዎችን ለማግኘት ማመልከቻ ለማስገባት በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ለሁሉም ሰራተኞች ድጋፍ ይሰጣል። ስራ በማቆም ለተጎዱ ሰራተኞች በምክር ቤቱ ውስጥ መልሶ የማሰማራት እድሎች ሊገኙ ይችላሉ። ልጆቻችንን እና ቤተሰቦቻችንን እንደምንደገፊው ሁሉ በዚህ ሽግግር ስራ የማቆም አደጋ ላይ ያሉ ሰራተኞች ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር ነው። ይህ የምክር ቤቱን የሰራተኛ ድጋፍ ፕሮግራም ማግኘትን፣ ሚስጥራዊ ምክር እና የምክር አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ የድጋፍ፣ የምክር እና የስልጠና እንቅስቃሴ ፕሮግራምን ይጨምራል።

በትምህርት ቤቱ ሕንፃ ላይ ለውጦች ይኖሩ ይሆን?
የSt Dominic ቦታ በከፊል በRCDOW እና በምክር ቤቱ ባለቤትነት ስር ነው። ትምህርት ቤቱ ከተዘጋ፣ ምክር ቤቱ እና ደብሩ ለወደፊት ስለሚኖረው የቦታ አጠቃቀም ተለዋጭ አማራጮችን ማሰብ ይኖርባቸዋል።

ቀጥሎ ምን ይሆናል?

ይህ ጽሁፍ የ St Dominic Catholic ትምህርት ቤትን የመዝጋት እቅድን በተመለከተ የሚደረግ የስድስት ሳምንት የህዝብ ምክክር አካል ነው። ምክክሩ በ8 ኦክቶበር ተጀምሮ በ19 ኖቬምበር 2024፣ 5pm ላይ ያበቃል።

ለምክሩ ምላሽ መስጠት የሚችሉባቸው ብዙ መንገዶች አሉ እነዚህም በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ ላይ ተቀምጠዋል።

ምክር ቤቱ በህግ የተጠየቁትን እቅዶች መልቀቅ ወይም አለመልቀቅን በተመለከተ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት በዚህ የምክክር ወቅት የቀረቡትን የሁሉንም አስተያየቶች ግምት ውስጥ ያስገባል። እቅዶቹ ከተለቀቁ፣ የማስረጃ መግለጫ ጊዜ ተብሎ የሚጠራ ተጨማሪ አስተያየቶች መቀበያ ጊዜ ይኖራል። ይህ ለ28 ቀናት ይቆያል። የመጨረሻ ውሳኔ በ Hackney ካቢኔ በቀጣይ ቀን የሚተላለፍ ይሆናል። የዚህ እቅድ የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ይታያል (ቀኖቹ ሊለወጡ ይችላሉ)።

የጊዜ ሰሌዳ

| ቀን | ዝግጅት |
|---|---|
| **8** ኦክቶበር **- 19** ኖቬምበር **2024** | መደበኛ ያልሆነ ምክክር<br><br>የወላጅ/የአሳዳጊ ስብሰባ ቀናት እና ተጨማሪ የተሳትፎ እድል ለብቻው በ St Dominic Catholic የመጀመሪያ ትምህርት ቤት የሚጸድቅ ይሆናል።<br><br>ትምህርት ቤቱ ለልጆች፣ ለወላጆች/ተንከባካቢዎች፣ ለሰራተኞች እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ለመረዳት ስለሚያግዘን የእርስዎ አስተያየት፣ ጥቆማቆች እና ግብረመልስ አስፈላጊ ናቸው። |
| ጃንዋሪ **2025** | መደበኛ ያልሆነ ምክክር ውጤቶች በHackney ካቢኔ ግምት ውስጥ ይገባሉ። ለ St Dominic's Catholic ትምህርት ቤት መዘጋት ህጋዊ ማስታወቂያ የመልቀቅ ወይም ያለመልቀቅ ውሳኔ ተላልፏል። |
| ፌብሩዋሪ **-** ማርች **2025** | ህጋዊ ማስታወቂያ ለ4 - ሳምንት የማስረጃ መግለጫ ጊዜ ታትሟል |
| ኤፕሪል **2025** | የማስረጃ መግለጫ ጊዜ ውጤት እና ማናቸውም ተቃውሞዎች በካቢኔው የታዩ ሲሆን የመዘጋት እቅዱ ላይ የመጨረሻው ውሳኔ ተላልፏል። |
| የበጋ ጊዜ **2025** | እቅዶቹ ከጸደቁ፣ የትምህርት ቤት መዘጋት ዝግጅቶች ተከናውነዋል (በካቢኔው ውሳኔ መሰረት)። |
| **31** ኦገስት **2025** | የSt Dominic's Catholic አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በይፋ ይዘጋል። |
| ሴፕቴምበር **2025** | የቀድሞ የ St Dominic ተማሪዎች በአዲሱ ትምህርት ቤቶቻቸው ትምህርት ይጀምራሉ። |

**ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?**

ስለዚህ እቅድ ከ Hackney Education ድረ ገጽ በ bit.ly/school-proposals ላይ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ

**ለዚህ ምክክር ምላሽ የምሰጠው እንዴት ነው?**

በዚህ እቅድ ላይ አስተያየቶችዎን መስጠት የሚችሉት በ፦

- ከዚህ የምክክር ሰነድ ጋር የተያያዘውን የምላሽ ቅጽ በመሙላት ወይም
- በመስመር ላይ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ ሊንክ ጠቅ በማድረግ፦bit.ly/school-proposal-consultation
- ወይም consultation.hackney.gov.ukን በመጎብኘት

የጽሁፍ ምላሽ ቅጽ ለመሙላት ከመረጡ፣ እባክዎን በ St Dominic ትምህርት ቤት ቢሮ ይስጡት ወይም ለሚከተለው በፖስታ ይላኩት፦

የHackney ምክር ቤት
የትምህርት አገልግሎቶች
የትምህርት ቤት ቦታ እቅድ
የHackney የአገልግሎት ማዕከል፣ 3rd Floor
1 Hillman Street
London, E8 1DY

የአስተያየቶች እና የጥቆማዎች ማብቂያ ቀን ማክሰኞ **19** ኖቬምበር **2024**፣ **5pm** ላይ ነው።

ስለዚህ እቅድ ማናቸውም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን ለ school.sufficiency@hackney.gov.uk ኢሜይል ይላኩ

ይህንን ሰነድ በተለየ ቅርጸት ከፈለጉ እባክዎን ያነጋግሩን እና በሚቀጥሉት አምስት የስራ ቀናት ውስጥ እንመልስሎታለን።

የተደራሽነት መግለጫ፦ ይህንን ሰነድ በተለየ ቅርጸት ከፈለጉ፣ እባክዎን ለ **school.sufficiency@hackney.gov.uk** ኢሜይል ይላኩ

የእርስዎን ጥያቄ ከግምት ውስጥ የምናስገባ ሲሆን በሚቀጥሉት አምስት የስራ ቀናት ውስጥ እንመልስሎታለን።

**If you would like to find out what this document says please tick the appropriate box, put your name, address and phone number at the bottom of this page and return it to the address below.**

☐ এই দলিলে কি লেখা আছে সে সম্পর্কে যদি আপনি জানতে চান তাহলে অনুগ্রহ করে উপযুক্ত বাক্সে টিক্ দিন, এই পাতার নীচে আপনার নাম, ঠিকানা ও ফোন নম্বর লিখুন এবং এটি নীচের ঠিকানায় ফেরত পাঠান। (Bengali)

☐ 如果你想知道這分文件的詳細內容，請在方框內打鉤，在本頁下面寫下你的名字、地址和電話號碼並寄到下面的地址。(Chinese)

☐ Si vous désirez connaître le contenu de ce document, veuillez cocher la case appropriée et indiquer votre nom, adresse et numéro de téléphone au bas de cette page et la renvoyer à l'adresse indiquée ci-dessous. (French)

☐ Ger hun dixwazin bizanibin ku ev dokument çi dibêje, ji kerema xwe qutîka minasib işaret bikin, nav, navnîşan û hejmara telefona xwe li jêrê rûpel binivîsin û wê ji navnîşana jêrîn re bişînin. (Kurdish)

☐ Jeśli chcesz dowiedzieć się, jaka jest treść tego dokumentu, zaznacz odpowiednie pole, wpisz swoje nazwisko, adres I nr telefonu w dolnej części niniejszej strony I przeslij na poniższy adres. (Polish)

☐ Haddii aad jeclaan lahayd in aad ogaato waxa dokumeentigani sheegayo fadlan calaamadi godka ku haboon, ku qor magacaaga, cinwaanka iyo telefoon lambarkaaga boggan dhankiisa hoose ka dibna ku celi cinwaanka hoose. (Somali)

☐ Si desea saber de lo que trata este documento, marque la casilla correspondiente, escriba su nombre, dirección y numero de teléfono al final de esta página y envíela a la siguiente dirección. (Spanish)

☐ Bu dökümanda ne anlatıldığını öğrenmek istiyorsanız, lütfen uygun kutuyu işaretleyerek, adınızı, adresinizi ve telefon numaranızı bu sayfanın alt kısmına yazıp, aşağıdaki adrese gönderin. (Turkish)

☐ اگر آپ یہ جاننا چاھتے ھیں کہ دستاویز میں کیا لکھاھےتو ازراہ کرم مناسب باکس میں صحیح کا نشان لگائےاوراپنا نام، پتہ اور فون نمبر اس صفحہ کے نیچےلکھئےاوراسے نیچے دیئے گیے پتہ پر واپس بھیج دیجئے– (Urdu)

☐ Nếu bạn muốn biết tài liệu này nói gì hãy đánh dấu vào hộp thích hợp, điền tên, địa chỉ và số điện thoại của bạn vào cuối trang này và gửi lại theo địa chỉ dưới đây. (Vietnamese)

☐ אויב ווילט איר וויסן וואָס דער דאָקומענט זאגט, ביטע טיק די פאסיגע קעסטל, שרייב דיין נאָמען, אַדרעס און טעלעפאָן נומער און שיק עס צוריק צו די אַדרעס אונטן. (Yiddish)

If you would like this document in any of the following formats or in another language not listed above, please complete and send the form to the address below. ☐ **In large print** ☐ **In Braille** ☐ **On disk** ☐ **On audio tape**

☐ **In another language, please state:** ______________________________

Name: ____________________________________________

Address: __________________________________________

Telephone: ________________________________________

Return to: **Freepost, LBH Consultation Team, Hackney Town Hall, Mare Street, London, E8 1EA**